AFRICAN COMMUNITIES TOGETHER

TPS-DED AAC

**የ ቲ.ፒ.ኤስ. (TPS) ጠቅላላ መግለጫ**

**የ ቲ.ፒ.ኤስ. (TPS) መነሻ፡**

ቲ.ፒ.ኤስ. (TPS) በዲፓርትመንት ኦፍ ሆምላንድ ሴኪዩሪቲ (DHS) የተሰጠ የሰብዓዊ ደህንነት ከለላ ማለትም ስደተኖች አገራቸው ላይ ባለው ሁኔታ ወደ አገራቸው ቢመለሱ በደህንነታቸው ላይ ችግር ሊያጋጥማቸው በሚችልበት ሁኔታ ላይ ሳሉ አስገድዶ ወደ አገራቸው የመመለስ አሰራር በጊዜያዊነት የሚያስቀር ነው። ይህም ከለላ ወይም ድንጋጌ በኮንግረስ የተወሰነ ሲሆን ሰዎች አገራቸው ውስጥ እየተካሄደ ባለ የትጥቅ ትግል፣ የተፈጥሮ አደጋዎች፣ ወይም ሌሎች ከባድ እና ጊዜያዊ የሆኑ ችግሮች ምክንያት ወደ አግራቸው ቢመለሱ ይሚገጥማቸውን የደህንነት አደጋ በመገንዘብ ነው። አንድ አገር ከላይ ከተጠቀሱት ችግሮች  አንዱ በተከሰተበት ጊዜ አገሪቱ በ ቲ.ፒ.ኤስ. (TPS) ልትመደብ ትችላለች። ከፍተኛ ማህበራዊና ሰባዊ ተሚጋቾች ግፊት ዲፓርትመንት ኦፍ ሆምላንድ ሴኪዩሪቲ (DHS)ን አንድን አገር በቲ.ፒ.ሴስ. (TPS) እንዲመድብ ይገፋፋል ወይንም ይረዳል።

**የ ቲ.ፒ.ሴስ. (TPS) ጥቅሞች:**

ምንም እንኳን ጊዜያዊ ቢሆንም፣ ቲ.ፒ.ኤስ. (TPS) ከለላው (ዋስትናው) እስከሚያበቃበት ጊዜ ድረስ ከአገር የመባረር ፍራቻ ሳይኖር በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በህጋዊ መንገድ የመኖር እና የስራ ፈቃድ የማግኘት መብት ይሰጣል። ቲ.ፒ.ኤስ. (TPS) ከለላ ብቁ ለመሆን የመጀመሪያው መስፈርት በዲፓርትመንት ኦፍ ሆምላንድ ሴኪዩሪቲ (DHS) ከተጠቀሰው ቀን በፊት በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ እንደነበሩ እና እንደሚኖሩ ማረጋገጥ ነው። ከለላው (ዋሰትናው) እስከ 18 ወራት ድረስ ሊቆይ ይችላል፣ ከዚያም በዲፓርትመንት ኦፍ ሆምላንድ ሴኪዩሪቲ (DHS) የአገሩን ሁኔታ ገምግሞ ከለላውን (ስያሜውን) ያራዝማል፣ ተደራሽነቱን ያሰፋል ወይም ስያሜውን ያቋርጣል።

የከለላው **(**ስያሜው**)** መራዘም፡  ጽህፈት ቤቱ ከለላውን (ስያሜውን) ሲያራዝም ከዚህ በፊት የተመዘገቡ ሰዎች እንደገና በመመዝገብ ከለላውን (ዋስትናውን) መቀጠል ይችላሉ። ጽህፈት ቤቱ ከለላውን ለምን ያህል ጊዜ እንደሚያራዝመው ይገልጻል፣  ይሄም መጀመሪያ ካሰቀመጠው ቀን ከ6 ወር፣ 12 ወር ወይም እስከ 18 ወር ሊያራዝመው ይችላል።

የከለላው **(**ስያሜው**)** መታደስ **(**እንደገና መሰየም**)**፡  አንዳንድ ጊዜ ጽህፈት ቤቱ አንድን ህገር ለቲ.ፒ.ሴስ. (TPS) እንደገና ለመሰየም ወይም ከለላ ለመስጠት ሊወስን ይችላል። በሚታደስበት (እንደገና በሚሰየምበት ጊዜ) በመጀመሪያ ጊዜ የተጥቀሰውን የአመልካጮች ወደ አሜሪካ የገቡበትን ቀነ ገደብ ሊያራዝም ይችላል። በዚህም መሰረት በተራዘመው አዲሱ የቀነ ገደብ መሰረት ተጨማሪ አዳዲስ ሰዎችን የዕድሉ ተጠቃሚ ሊያደርግ ይችላል።

የከለላው መቆም**/**መቋረጥ፡ የከለላው ስያሜ ጊዜ ሊያበቃ (ሊያልቅ) 60 ቀናቶች ሲቀሩት ጽህፈት ቤቱ በህገሪቱ ያለውን ነባራዊ ሁኔታዎች  በህግ የተቀመጡትን መስፈርቶች ሚሟላትና አለሚሟላታቸውን እና ሰዎች ወደ ህገራቸው ሲመለሱ ደህንነታቸው አደጋ ላይ መውደቅና አለመውደቁን ይገመግማል።  በግምገማው መሰረት ጽህፈት ቤቱ የቲ.ፒ.ኤስ. (TPS) ከለላ መቀጠል አስፈላጊነት ካላመነበት ከለላውን (ስያሜውን) ማቆም ይችላል።

- ስያሜው **(**ከለላው**)** ሲቋረጥ ምን ይሆናል**?** ስያሜው (ከለላው) የማለቂያ ቀነ ገደቡ በሚጠጋበት ጊዜ፣ ዲፓርትመንት ኦፍ ሆምላንድ ሴኪዩሪቲ (DHS) የከለላው ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎችን የከለላው ጊዜ የማለቂያው ጊዜ እየተቃረበ መሆኑንና ከማለቁ በፊት አንዳንድ ዝግጅቶችን እንዲያደርጉ ያሰታውሳል። ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፡- ሌላ ህጋዊ መኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት ማመቻቸት፣ ወደ ትውልድ አገራቸው ለመመለስ ማቀድ፣ ወደ ሌላ ህገር መዘዋወር፣ ወይም ከማህበራዊ ወይም ከሰብዓዊ ንቅንቅቄ ቡድኖችን ጋር በመደራጀት ለቋሚ ከለላ ወይም ሌላ አይነት ተመሳሳይ ከለላ ለማግኘት ጥረት ማድርግ።

ቋሚ ከለላ ለማግኘት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች፡

በአገሪቷ ውስጥ ከ100 በላይ የሆኑ ድርጅቶች በተናጠል ወይም በጋራ በመሆን ለሁሉም የ ቲ.ፒ.ኤስ. (TPS) ከለላ ላላቸው ሰዎች ቋሚ የከለላ ስያሜ እንዲሰጣቸው ይሚገታሉ። እነዚህም ተሚጋቾች ለዋይት ሀውስ፣ ለዲፓርትመንት ኦፍ ሆምላንድ ሴኪዩሪቲ (DHS)፣ ለዲፓርትመንት ኦፍ ስቴት እና ከስቴት እና ከአካባቢው ለተመረጡ ባለስልጣናት ግንዛቤ ይሰጣሉ ወይም ቅስቀሳውን ያደርጋሉ ። ትልቁ ግባቸው (ዓላማቸው) ለስደተኞች ቋሚ የሆነ ከለላ ማግኘት ቢሆንም በተጓዳኝ ለስደተኞች ሴፍቲኔት (ደህንነት) ሲባል የቲ.ፒ.ኤስ. (TPS) ተደራሽነት እንዲስፋፋ መስራት ነው።

በአሁኑ ጊዜ የቲ.ፒ.ኤስ. **(TPS)** ስያሜ **(**ከለላ ያላቸው**)** አገሮች፡

በአሁኑ ጊዜ ለቲ.ፒ.ሴስ. (TPS) ስያሜ የተመደቡት አገሮች ደቡብ ሱዳን፣ ሶማሊያ፣ የመን፣ ካሜሩን፣ አፍጋኒስታን፣ ዩክሬን፣ ሶሪያ፣ ቬንዙዌላ፣ በርማ፣ ኤል ሳልቫዶር፣ ሆንዱራስ፣ ኒካራጓ፣ ኔፓል፣ ሄይቲ፣ ሱዳን እና ኢትዮጵያን ያካትታል። በአጠቃላይ የቲ.ፒ.ኤስ. (TPS) ከለላ ተጠቃሚዎች ወደ 500,000 የሚገመቱ ሲሆኑ አሁን ደግሞ ተጨማሪ 30,000 ኢትዮጵያውያን በቅርቡ በተሰጠው የከለላ ውሳኔ መሰረት ብቁ ሆነዋል።

---

TPS-DED AAC በአገሪቷ ከ100 በላይ በ TPS ሕግ እና ፖሊሲ ጠበብት የሆኑ ድርጅቶችን ያካተተ ጥምረት ነው። አባል ድርጅቶቹ በአሜሪካ ውስጥ የሚኖሩ ተጠቂዎችን ከሚያገለግሉ ማህበራት ጀምሮ እስከ በ TPS በተካተቱ አገራት ውስጥ ይሚሰሩ እና የዚያን አገር ጥልቅ መረጃ የሚሰጡ ከአለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ያካትታል።

አድራሻችን : admin@masade.com